የሰ/መ/ቁ. 46281

ታህሣሥ 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራ ወርቅ ጠበቃ ተስፋዬ ርቀቱ ቀረበ

ተጠሪ፣ ይገረም ፈዬ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ከተወሰነ በኃላ ክሱን ሲመሠረት የከፈለውን የዳኝነት ገንዘብ ተጠሪ ትተካለት የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ተጠሪ ክስ የመሠረተው ብር 30,000 ግምት ያለው ባህር ዛፍ ቆርጣ ስለወሰደችብኝ ገንዘቡን ትክፍለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ ክሱን በመካድ የተከራከረች ሲሆን ፍ/ቤቱም የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ይግባኙን ለሚሰማው የበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ለክሱ ምክንያት የሆነው ባህርዛፍ ስለመቆረጡ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አትከፍልም በማለት በአንድ በኩል ሲወስን በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ብር 1718.50 አመልካች ትተካለት ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር በጭብጥነት ከተያዘው ነጥብ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተቀባይነትን አላገኘም፡፡ ክሱ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በመደረጉም በክሱ የተመለከተውን ብር 30,000 አመልካች ልትከፍልህ አይገባም ተብሎ ተወስኖአል፡፡ ለዳኝነት ተከፈለ የተባለው ብር 1718.50 ሊከፈል የቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 215 መሠረት ነው በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክሶች ሁሉ ዳኝነት ሊከፈልባቸው እንደሚገባ በተጠቀሰው ቁጥር 215/1 አመልክቶአል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የቻልነው

የዳኝነት ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የከሣሹ ወገን እንደሆነ ነው በእርግጥ በክርክር ወቅት ወይም ክርክሩን ለማካሄድ የሚወጡ ወጪዎች ስለወጪና ኪሣራ በሚመለከት በተደነገገው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በስምንተኛው መጽሐፍ ሥር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር እየታዩ በየትኛው ተከራካሪ ወገን እንደሚሸፈኑ በፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ ቁ 462 እንደተመለከተው በሌላ አኳኋን በግልፅ ካልተደነገገ በቀር በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሣራ የትኛው ወገን ሊከፍለው እንደሚገባ ፍ/ቤቱ ተገቢ በመሰለው ሁኔታ ሊወሰን ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ያለአግባብ በአመልካች ላይ ክስ መመስረቱ ተረጋግጦ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ከመወሰኑ አልፎ በአመልካች በኩል የተፈጸመ ኪሣራ ሊያስከፍል የሚችል ድርጊት /ጥፋት/ ስለመኖሩ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አልተመለከተም ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ለተጠሪ ኪሣራ የምትከፍልበት የሕግ አግባብ አይኖርም ሕግ ሳይፈቅድ ረቺ የሆነውን ወገን ለተረቺ ኪሣራ እንዲከፍል መወሰን ደግሞ ሕጉን በተሳሳተ ሁኔታ መተረጎም ወይም መተግበር ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጋምቤላ ሕዝቦች ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ28/07/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የዳኝነት ገንዘቡን እንድትተካ የምትገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ